# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የዓቢይ ጾም ሦስተኛው ሰንበት «ምኩራብ» ይባላል።

## የዕለቱ ምስባክ

እስመ ቅንዓተ ቤተከ በልዓኒ
ትዕይርቶሙ ለእለ ይትኤየሩከ ወድቀ ላዕሌየ
ወቀጻእክዋ በጾም ለነፍስየ

የቤትህ ቅናት በልቶኛል
የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ላይ ወደቀ
ነፍስን በጾም አስመረርኩአት (ቀጣኋት)

መዝ ፷፰፥፱

ትርጉም፥ በቤተ መቅደስህ ገበያ አቁመውበት አይቼ የቀናሁት ቅንአት እንደ እሳት አቃጠለኝ (ትዕይርቶሙ) አንተን በቤተ መቅደስህ ገበያ አድርገው እንደተገዳደሩህ እኔም ገበያውን ብትፈታላቸው «መኑ አብሐከ ትግበር ዘንተ - ይህን እንድታደርግ ማን ስልጣን ሰጠህ» አሉኝ (ዮሐ 2፥8)። እንዲሁም አንተን መና ከደመና አውርደህ ብትመግባቸው «ምንት ጣዕሙ ለዝ መና» ብለው እንደተገዳደሩህ እኔንም «የሰው ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም» ብላቸው «እንበላው ዘንድ ሥጋውን ሊሰጠን እንዴት ይችላል» ብለው ተፈታተኑኝ (ዘጸ ፲፮፥፲፭ ። ዮሐ ፮፥፶፪) ሰውነቴን በጾም አደከምኳት ጌታ ዓርባ ቀንና ሌሊት ጾሟል (ዘጸ ፴፬፥፳፰ እስከ ፍጻሜው ። ማቴ ፬፥፪-፮)።

**ወንጌል፥** ዮሐ ፪፥፲፪ እስከ ፍጻሜው
**ቅዳሴ፥** የጌታችን (ነአኵተከ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ቦአ ኢየሱስ ምኩራብ አይሁድ
(ኢየሱስ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገባ)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ቆላ ፪፥፲፮ እስከ ፍጻሜው | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፪፥፲፬ እስከ ፍጻሜው | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፥፩-፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

የዚህ ዕለት ስያሜ ምኩራብ ይባላል። መድኃኒታችን በምኩራብ አይሁድ ተገኝቶ ለታሰሩት ነጻነትን ለሞቱት ሕይወትን ለድሆች ወንጌልን ለተጠቁት ነጻነትን በፍርድ ላሉት ሁሉ ዓመተ-ምሕረትን ስለማስተማሩ በትምህርቱም ስለመደነቁ ይነገራል፤ ይዘመራል። ስያሜው የቅዱስ ያሬድ ነው። መድኃኒታችን በምኩራብ የሰራቸውን ነገሮች እያሳታወሰ ስለዘመረ ዕለቱ ምኩራብ ተባለ ይህም የዓቢይ ጾም ሦስተኛ ሰንበት ነው።

## የዕለቱ ትምህርት

# የቤትህ ቅናት በላኝ

ስለ ቤተ መቅደስ ክብር እና ምንነት የመስከረም ወር ፬ኛ ሰንበትን ትምህርት ይመልከቱ። ምኩራብ ከቤተ መቅደስ በብዙ ያለያል ቤተ መቅደስ በብሉይ ኪዳን ከኢየሩሳሌም ውጭ አይሰራም ነበር። ምኩራብ ግን በየትኛውም ቦታ መስራት ይቻል ነበር። የሚሰራበትም ዓለማ ለሕገ ኦሪት መማሪያ ቃለ እግዚአብሔር መንገሪያ ነበር። በዚህ ዕለት ቅዱስ ያሬድ በመዝሙር ጌታ በምኩራብ ገብቶ ስለማስተማሩ ዘምቷል።

ጥቅስ በግዕዝ፥ ቦአ ኢየሱስ ምኩራብ አይሁድ ወመሐረ ቃለ ሃይማኖት ወይቤሎሙ ምጽዋት አበድር እመከዋት አነ ውእቱ እግዚአ ለሰንበት ወአቡሃ ለምህረት ኢትግበሩ ቤተ አቡዬ ቤተ ምስያጥ ምስየሰ ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ትሰመይ ቦአ ምኩራቦሙ ልገሠጸሙ ያርምሙ አንብሩ ምሂሮቶ ሞገሰ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ መሳዕስአ አፉሁ።

ትርጉም፥ «ኢየሱስ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገባ የሃይማኖትን ቃል አስተማሩ ከመስዋእት ምዋትን እወዳለሁ አላቸው። የሰንበት ጌታዋ የምሕረት አባትዋ እኔ ነኝ አላቸው። የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉ ቤቴ የጸሎት ቤት ነው (ይባላል)። ምኩራብ ገብቶ ተቆጣቸው ዝም ይሉ ዘንድ ትምህርቱን የቃሉን ሞገስ (መወደድ) የነገሩን መወደድ የአፉን ለዛ አደነቁ» ብሎ መድኃኒታችን በምኩራብ ማስተማሩን ቅዱስ ያሬድ ዘመረ።

ወንጌላዊው ማቴዎስም «ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝቡም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር» ብሎ ከቅዱስ ያሬድ ቀድሞ ተናገረ። አይሁድ ፊት ለፊት ለታይታ ለከንቱ ውዳሴ በሚቀመጡበት ምኩራብ ክርስቶስ የነጻነትን ወንጌል እንደሰበከ ወንጌላዊው ሉቃስም «ኢየሱስም … ወዳደገበት ወደ ናዝሬት መጣ። እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ ሊያነብም ተነሳ። የነብዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት። መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታተን ለእውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» ተብሎ የተጻፈውን ሥፍራ አገኘ። መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኩራብም የነበሩት ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር። እርሱም፥ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር። ከአፉ ከሚወጣው ከጸጋው ቃል የተነሳ እየተደነቁ «ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? ይሉ ነበር» ብሎ ጽፎልናል (ሉቃ ፬፥፲፬-፳፫)።

በቅዳሴ ጊዜም የተነበበው ወንጌልም በቤተ መቅደስ የሚፈጸመው የንግድ ሥራ እንዳሳዘነው ገልጦ በጅራፍ መንጋዎቹን ከነጋዴዎቻቸው ጋር ከቤተ መቅደስ እንዳስወጣና «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን እኔ እሰራዋለሁ (እስነሳዋለሁ)» ብሎ ስለሞቱና ትንሣኤው እንደተናገረ ይተርካል። በትምህርቱ የተማረኩ ሰዎች ቢያምኑበትም የሰውን ልብ የሚያውቅ ጌታ የልባቸውን አይቶ እንደ አልተቀበላቸውም «አይፈቅድ ይንግርዎ ግዕዞ ለሰብእ እስመ ላሊሁ የአምሮ ለሰብእ» ስለ ሰው ማንነት ሊነግሩት አያሻውም እርሱ ራሱ ሰውን ያውቀዋልና ብሎ ዮሐንስ እንደተናገረ ተጽፏል።

ወዳጄ ሆይ፥ ሕይወትህ ቤተ መቅደስ የኃጢአት ገበያ እንዳይሆን ተጠንቀቅ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።